በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

## *ፕሮቴስታንት*

## ክፍል  አምስት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
መጋቢት ፱  ቀን  ፳፻፩  ዓ.ም.

## #ፕሮቴስታንቶች;

- ሉተር የተማረ የካቶሊክ መነኩሴ ነበር፡፡

- የሉተር የተቃውሞው ዓላማ የካቶሊክን ሥርዓተ እምነት ማሻሻል ወይም ማደስ እንደ ነበር በተከታዮቹ ይነገርለታል፡፡

- ሉተር 1516 ዓ.ም. የሮም ለሚገኘው የጴጥሮስ #ሕንጻ; ግንባታ ገቢ ለማሰባሰብ በፓፑ አማካይነት ለቀደመውም ለወደፊቱ የኃጢአት ሥርየት እያሉ ገንዘብ ሲሰበስቡ ተመለከተ፡፡ አለመግባባቱም እየሰፋ ሄደ፡፡ የካቶሊክንም ትምህርት ተቃውሞ በጀርመን የካቶሊክ ቤተ-ጸሎት 95 ቴሲስ ጽፎ በመለጠፉ ምክንያት ተመሰረተ፡፡

- ብዙ ተከታዮችም ስላፈራ ከካቶሊክ ተለይቶ ወጣ፡፡ በዚህም የተነሳ እርሱና ተከታዮቹ ፕሮቴስታንት ተባሉ፡፡ ተቃዋሚዎች ማለት ነው፡፡ ይህም የሆነው በ1517 ዓ.ም. ነበር፡፡

- በሌሎች አገሮች የሚገኙትም እነ ጆን ካልቪን የርሱን መንገድ ተከተሉ፡፡

- ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ሰው አንብቦ ሊረዳው ስለሚችል መተርጉማን አያስፈልጉትም በሚል መርሆ እየተሳቡ ከማን አንሼ በሚል መመሪያ በፕሮቴስታንት ውስጥ ውዝግብ ተፈጥሮ በእምነትና በሥርዓት የማይመሳሰሉ በሺህ የሚቆጠሩ ክፍሎች ተፈጥረዋል፡፡ ተከታዮቹም ሉተራውያን ይባላሉ፡፡ ለራሳቸው አካባቢውን ሊስብ የሚችል ስያሜ እየሰጡ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክንን በጎች ይነጥቃሉ፡፡

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የፕሮቴስታንት ልዩነት

በፕሮቴስታንቶች ከትውፊተ ቤ/ክ የወጣ የተሳሳተ መንገድ የተነሳ የምንለያይባቸው የእምነት መሠረቶች ወይም ትምህርቶች

1. የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት
2. የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት
3. ምስጢራተ ቤተክርስቲያን
4. ጥምቀት
5. ታቦት
6. ትውፊተ ቤተክርስቲያን
7. ጾም
8. መስቀል
9. አማላጅነትና የቅዱሳን መታሰቢያ
10. ጸሎተ ፍትሐት
11. እምነትና ሥራ ወዘተ…

# <u>የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የፕሮቴስታንት ልዩነት</u>

## <u>ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን</u>

1. በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት እናምናለን፡፡ በተዋሕዶ አንድ የሆኑ መለኮትና ሥጋ ለዓይን ቅጽበት እንኳን ተለያይተው አያውቁም፡፡ <u>ዮሐ 1፡1-14 ፤ ቆላ 2፡9 ፤ ሮሜ 1፡20</u>
2. መንፈስቅዱስ ከአብ ሠረጸ ብለን እናምናለን፡፡ <u>ዮሐ 15፡26፡፡</u>
3. በሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን እናምናለን፡፡ <u>ምሳሌ 9፤1፡፡</u>
4. ጥምቀት ለድኅነታችን፤ ስለ ኃጢአት ስርየት፤ ከበደላችን ለመንጻጽ፤ ከክርስቶስ ጋር ሞተን ለመነሳት ነው፡፡ <u>ማቴ 28፡19፤ ማር 16፡16፤ የሐ. ሥራ 2፡38፤ 1ኛ ቆሮ 6፡11፤ የሐ. ሥራ 22፡16፤ ሮሜ 6፡2-6፤ ገላ 3፡27፤ ኤፌ 5፡26፤ ቲቶ 3፡5፡፡</u>
5. ታቦት የእግዚአብሔር ዙፋን - ማደሪያ ነው፡፡ በምድርም በሰማይም አለ፡፡ <u>ዘጸአት 25፡22፤ ዘኁልቁ 7፡89፤ ዘዳግም 10፡1፤ ኢያ 3፡3-6፤ ራዕይ 11፡19፡፡</u>
6. የሐዋርያትን የአንዲቱን ቤ/ክ ትውፊት ትጠብቃለች፡፡ <u>2ኛ ተሰ 2፡15፤ ዕብ 11፡14፡፡</u>
7. አጽዋማት በቤ/ክ ይወሰናሉ፤ በራስ ፈቃድ የነፍስ አባትን ምክር በመጠየቅ ወይም ቀኖናም በመቀበል ይጾማል፤ በጾም ወቅትም ሥጋና የእንስሳት ተዋጽኦን መመገብ አይፈቀድም፡፡ <u>ሕዝ 4፡1-ፍጻ.፤ ነገ ቀዳ. 20፡9-12፤ መዝ 109፤24</u>፡፡
8. መስቀል የሃይማኖታችን ምልክት ነው፡፡ <u>ገላ 6፡14፤ ፊል 3፡18</u>፡፡
9. ቅዱሳን ያማልዱናል መታሰቢያቸውንም እናደርጋለን፡፡ <u>ኢሳ 56፡1-7፤ ዕዝራ 6፡10፤ ኢዮ 42፡10፤ ዘፍጥ 20፡7፡፡</u>
10. ለሙታን ነፍሳቸውን ይምር ዘንድ እንጸልያለን፡፡ <u>1ኛ ሳሙ 2፡6፤ መዝ 16፡10፤ መዝ 30፡2፤ መዝ 49፡15፤ሉቃስ 16፡19-31፡፡</u>
11. እምነት ብቻ ሳይሆን ሥራም ያስፈልጋል፡፡ <u>ያዕ 2፡ 17፡፡</u> ወዘተ…

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የፕሮቴስታንት ልዩነት

## ፕሮቴስታንቶች

1. መለኮትና ሥጋ ብለው ከፋፍለው እንደ ኬሎቄዶናውያን በኢየሱስ እናምናለን ይላሉ።
2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የሠረጸ ነው ይላሉ። ዮሐ 15፡26 ይህን አይልም።
3. ምስጢራተ ቤተክርስቲያን፤ ትውፊት የሚባል የላቸውም።
4. ጥምቀት ምልክት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ።
5. ጥምቀት ካደጉ በኋላ ብቻ ይፈጸማል። ሳይጠመቁ ለመሞት ዕድል ይሰጣል። የሐ. ሥ 16፡33።
6. ጥምቀትም በራስ ላይ ውሃ በማፍሰስ ይፈጸማል። ይህም በመዘፈቅ ከተጠመቀው ከጌታችንና ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጥምቀት ይለያል። ማቴ 3፡13-17፤ የሐ ሥራ 8፡37-39።
7. ማንኛውም ሰው (ወንዱም ሴቱም) ቄስ ነው። ጌታችን ግን እመቤታችንን እንኳን ለዚህ…
8. ኃጢአትን ለካህናት አይናዘዙም። ማቴ 16፡19፤ የሐ ሥራ 19፡18። ግን ይህን አያስተምርም።
9. ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ አማናዊውን ይሆናል ብለው አያምኑም።ዮሐ 6፡50-58 ግን አይልም።
10. ቅዱስ ቁርባን፤ ዕጣን … የቤተመቅደስ አገልግሎት የለም። ራዕይ 5፡8።
11. የተወሰኑ አጽዋማት የላቸውም። ጾሙ ለተወሰኑ ሰዓታት መቆየት ብቻ ነው። በጾም ወተት መጠጣት፤ ሥጋ መብላት ይቻላል። በትውፊትም በመጽሐፍም አልተፈቀደም። ሕዝ 4፡1-ፍጻሜ
12. ጳጳሳት የሉአቸውም። ጋብቻ በሽማግሌዎቻቸው የሚፈጸም ውል ወይም ኮንትራት ነው።
13. በቅዱሳን አማላጅነት፤ በሚደረግላቸው መታሰቢያ… አያምኑም።

ይቀጥላል

… ከክፍፍሎቹ መካከል አንዳንዶቹን እንመልከት…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።